

# “ለአባቴ የሞት ፍርድ”

በሰሜን ኢትዮጵያ ለተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሜታ ያደረገው አስተዋጽኦ

AMNESTY INTERNATIONAL

አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ 10 ሚሊዮን ህዝብ አባላት ያሉት በሁሉም ሰው ውስጥ ያለን ሰብአዊነት የሚያንቀሳቅስ እና ሁላችንም የሰብአዊ መብቶቻችንን እንድናጣጥም ለለውጥ የሚያነሳሳ ዓለም ዓቀፋዊ እንቅስቃሴ ነው። ራዕያችን ባለስልጣናት የገቡትን ቃል የሚጠብቁበት፣ ዓለም አቀፍ ህግን የሚያከብሩበት እና በህግ የሚጠየቁበት ዓለም ነው።

ከማንኛውም መንግስት፣ ፖለቲካዊ ርዕዮተአለም፣ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ወይም ሀይማኖት ነፃ ነን፤ የገንዘብ ምንጫችንም በዋናነት ከአባላቶቻችን እና ከግለሰቦች የምናገኘው ልገሳ ነው። በሁሉም ቦታ ካሉ ሰዎች ጋር በአብሮነት እና በመተሳሰብ መስራት

© Amnesty International 2023
Except where otherwise noted, content in this document is licensed under a Creative Commons (attribution, non-commercial, no derivatives, international 4.0) licence.
https://creativecommons.org/licenses/by-nc-nd/4.0/legalcode
For more information please visit the permissions page on our website: www.amnesty.org
Where material is attributed to a copyright owner other than Amnesty International this material is not subject to the Creative Commons licence.
First published in 2023
by Amnesty International Ltd
Peter Benenson House, 1 Easton Street
London WC1X 0DW, UK

**ጠቋሚ: AFR 25/7292/2023**
**መነሻ ቋንቋ፤ እንግሊዝኛ**

**amnesty.org**

***የሽፋን ስዕል፤*** *ማበራሪያ/መግለጫ በአሊና ፔቼንኪና*

AMNESTY INTERNATIONAL

# ህብረተሰባችንን ወደተሻለ ሁኔታ ሊለውጠው ይችላል ብለን እናምናለን።

# ማውጫ


1. **ዋና ዋና ማጣቃለያ** ........ 4
2. ማጣቃለያ እና ምክረ ሃሳቦች ........ 10

ማጣቃለያ ........ 10

**ምክረ-ሃሳቦች** ........ 12

**ለሜታ** ........ 12

አሜሪካ፣ አየርላንድ እና እንደ አውሮፓ ህብረት ያሉ የክልል አካላትን ጨምሮ ለሜታ እንደ ዋና መቀመጫ የሚያገለግሉ መንግስታት ........ 13


**“ለአባቴ የሞት ፍርድ”**

በሰሜን ኢትዮጵያ ለደረሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሜታ ያደረገው አስተዋጽኦ

አምነስቲ ኢንተርናሽናል

# ፲. ዋና ዋና ማጠቃለያ

“አባቴ ላይ የተላለፈ የሞት ፍርድ እንደሆነ ታውቆኝ ነበር” አብርሃም ማዕረግ፣ በአባቱ በፕሮፌሰር ማዕረግ አማረ ላይ በትግራይ ተወላጅነታቸው ላይ ያነጣጠሩ በፌስቡክ የተለጠፉ ጽሁፎችን ሲያይ የተሰማውን ስሜት ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል የገለጸበት ቃል ነበር። ጽሁፎቹ፣ የፕሮፌሰር ማዕረግ አማረን ስም፣ ፎቶ፣ የስራ ቦታ የያዙ እና ፕሮፌሰሩም ከህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) ጋር ቁርኝት እንዳላቸው የሚወነጅሉ ነበሩ።

የሚያሳዝነው፣ አብርሃም ቀልቡ የነገረው ነገር ትክክል ነበር። ጽሁፎቹ ከተሰራጩ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ፣ ፕሮፌሰር ማዕረግ አማረ ጥቅምት 24 ቀን 2014 ከቤታቸው ደጃፍ ተገደሉ። ይህ የሆነው፣ አብርሃም እነዚህን ፅሁፎች በሜታ የሪፖርት ማቅረቢያ ፕላትፎርም (Meta Platforms reporting function) አማካኝነት ያልተሳካ ተደጋጋሚ ሙከራ እያደረገ ባለበት ሁኔታ ነበር።

ጥቅምት 25 ቀን 2013 ዓ.ም በትግራይ ክልል፣ በኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት ኃይሎች እና ከትግራይ ክልል መንግስት ጋር ትስስር ባላቸው ኃይሎች መካከል የትጥቅ ግጭት ተቀሰቀሰ፤ ቆይቶም ወደ አጎራባች አማራ እና አፋር ክልሎች ተዛመተ። በግጭቱም ወቅት የግጭቱ ተዋናይ የሆኑ አካላት ሁሉ በሰላማዊ ሰዎች ላይ ከፍተኛ የጭካኔ ተግባር ፈፀሙ።

ግጭቱ ከተቀሰቀሰ ከአንድ ሳምንት በኋላ፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በምዕራብ ትግራይ ማይ-ካድራ ከተማ በርካታ ሰላማዊ ሰዎች መገደላቸውን የሚያሳይ ዘገባ አወጣ። አምነስቲ ኢንተርናሽናል እና ሂውማን ራይትስ ዎች በምዕራብ ትግራይ ክልል፣ በትግራይ ተወላጆች ላይ የጦር ወንጀሎችና በሰብዐዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፤ የብሄር ማፅዳትን ጨምሮ፤ መፈጸማቸውን አረጋግጠዋል። እነዚህ ወንጀሎች የተፈጸሙትም ከአጎራባች የአማራ ክልል በተውጣጡ የክልል ባለስልጣናት እና የጸጥታ ኃይሎች፣ ምናልባትም በኢትዮጵያ ፌዴራል ኃይሎች ድጋፍና ተሳትፎ መሆኑን ዘግበዋል።

ጥቃቱ፣ የትግራይ ክልልን ጨምሮ በሰሜን ኢትዮጵያ ግጭቱ በተፋፋመባቸው አካባቢዎች በሚኖሩ ሰላማዊ ዜጎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል። በግምቶች መሰረት ግጭቱ 600,000 ገደማ የሚደርሱ የንፁሃን ዜጎች ህይወት ከመቅጠፉም በላይ፣ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ከቀያቸው እንዲፈናቀሉ ምክንያት ሆኗል። ከዚህም በላይ፣ 70,000 ገደማ የሚሆኑ ሰዎች በምስራቅ ሱዳን በሚገኙ የስደተኛ ካምፖች ውስጥ ተጠልለው ይገኛሉ።

በግጭቱ ወቅት፣የሜታ ንብረት የሆነው ፌስቡክ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ብጥብጥን በሚቀሰቅሱ እና ጥላቻን በሚያበረታቱ ይዘቶች ተጥለቅልቆ ነበር። በኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ፣ በመንግስት ደጋፊዎች እንዲሁም የመንግስት ደጋፊ በሆኑ የዜና ገፆች

አማካኝነት፣ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ ጥቃትና ዘረኝነትን የሚቀሰቅሱ እና ጥላቻን የሚያበረታቱ፣ በተለይ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ ያነጣጠሩ መልዕከቶችን ፌሰቡክ ላይ ለጥፈዋል። የእነዚህ መልዕክቶች ይዘት ደግሞ፣ የትግራይ ተወላጆችን ለኢትዮጵያ መረጋጋትና ጸጥታ አስጊ አድርገው የሚያሳዩ ነበሩ። ሁከትና ዘረኝነትን የሚቀሰቅሱ እና በትግራይ ማህበረሰብ ላይ ያነጣጠሩ ሌሎች ሰብአዊነት የጎደላቸው እና አድሏዊነት ያላቸው ይዘቶች ስርጭት ቀድሞውንም በቋፍ ላይ ያለውንና በጎሳ ጽንፈኝነት የተቃቃረው ማህበረሰብ ላይ ይበልጥ ነዳጅ አርከፍክፎበታል።

እነዚህ አደገኛ መልዕክቶች በፍጥነት ሊሰራጩ የቻሉትም ክትትልን መሰረቱ ባደረገ የንግድ ሞዴል አማካኝነት ነው። ይህ ሞዴል፣ የሰዎችን መረጃ በመሰብሰብ፣ በመተንተን እና በመጠቀም ላይ ተመርኩዞ የተገኘውን አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም ሰዎችን የፌሰቡክ ተሳታፊ ማድረግ ነው። የዚህ የንግድ ሞዴል ዋነኛ አላማ ሰዎችን [የንግድ] ማስታወቂያዎች ኢላማ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፤ ይህንን የሚያደርገው ደግሞ፣ ሰዎች ተጨማሪ መረጃን በመቃረም ስራ ተጠምደው በተቻለ መጠን በመድረኩ ላይ እንዲቆዩ በማማለል ነው። ዓላማውንም ለማሳካት፣ ይዘትን የሚቀርፁ አልጎሪዝሞች ተሳትፎን ከፍ ለማድረግ እና ብዙውን ጊዜ የሚያነቃቃ፣ ጎጂ እና መለያየትን የሚፈጥር ይዘት ለማጎልበት ተመቻችተው የተቀመሩ ናቸው፤ይህም በተጠቃሚዎች ዘንድ የበለጠ ትኩረትን የሚስብ ነው።በሰሜናዊ ኢትዮጵያ ግጭት አውድ ውስጥ፣ እነዚህ አልጎሪዝሞች በሰብአዊ መብቶች ላይ አፍራሽ ተጽኖዎች ነበሯቸው፤ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ ያነጣጠሩ መልዕከቶችን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ በጣም ተወዳጅ በሆነው በፌስቡክ ማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት፣ ጥላቻን ያዘሉ እና አመፅን፣ ጠላትነትን እና ዘረኝነትን የሚያበረታቱ መልዕከቶች ጎልተው እንዲሰራጩ አድርገዋል።

ኢትዮጵያውያን ጋዜጠኞች እና ተመራማሪዎችም የትጥቅ ግጭቱን የመሰነድ እና የመዘገብ ስራቸውን በመስራታቸው ብቻ፣ በፌስቡክ የተለቀቁ የጥላቻ ናዳ ይወርድባቸዋል። ኢትዮጵያዊቷ ጋዜጠኛ፣ ሉሲ ካሳ ብርሃን፣ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደገለፀችው፣ ትግራይ ውስጥ በመንግስት ታጣቂዎች የተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ረገጣዎችን መዘገቧን ተከተሎ፣ የተቃጡባትን የዛቻ ልጥፎችን ሽሽት ሀገር ጥላ ወደ ናይሮቢ ጠፍታ ነበር። ያም ሆኖ፣ ኬንያም እያለች የሜታ አልጎሪዝም ከሚያስከትለው መዘዝ አላመለጠችም። ትግራይ ውስጥ፣ የተቀጣጣይ የጦር መሳሪያ ጥቃት ሊሰነዘር እንደሚችል መዘገቧን ተከተሎ፣ እንደገና የዛቻ ኢላማ ሆነች፤ ያኔ፣ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ተከታዮች ያሉት የመንግስት አካውንት ፎቶዋን በመለጠፍ ተይዛ እንድትታሰር ጥሪ አቅርቦ ነበር። ልጥፉ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ “ላይኮችን” አግኝቷል፤ አስተያየትም ተሰጥቶበታል። ሉሲ፣ ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል እንደተናገረችው፣ “…መንግስት እና ተሰሚነት ያላቸው አክቲቪስቶች በድንጋይ መወገር እንዳለብኝ እና መንግስት በእርሷ ላይ “አንድ ነገር ያድርግ” እያሉ የሃይል እርምጃ እንዲወሰድብኝ ጥሪ ያቀርቡ ነበር። በዚህ የተነሳ፣ በናይሮቢ መቆየቴ አስተማማኝ አልነበረም።”

በዚህ ምክንያት፣ ሉሲ ዳግም ለመሰደድ ተገደደች፤ በኢንተርኔት አማካኝነት የተፈፀመባት ጥቃት በአዕምሮዋ ላይ ያደረሰውን ተጽእኖ ለመቋቋም ረጅም ጊዜ እንደፈጀባትም ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል ተናግራለች።

በሚያዝያ ወር 2012 ዓ.ም፣ በሰሜን ኢትዮጵያ የትጥቅ ግጭት ከመቀስቀሱ በፊት፣ ‘የተባበሩት መንግስታት የአመለካከት እና ሃሳብን የመግለፅ መብትን የማሳደግ እና የማስጠበቅ ልዩ ዘጋቢ’፣ የፌስቡክ መድረክ ለኢትዮጵያ የመረጃ ሥነ-ምህዳር ያለውን ጠቀሜታ በመጥቀስ እንዲህ ሲሉ መክረዋል፤ “የጥላቻ እና የሃሰተኛ መረጃ ማሰራጫ መድረክ ከመሆን ይልቅ፣ መድረኩ ሰዎች ሃሰባቸውን ለመገለፅ የሚያስችል ድጋፍ፣ [ሜታ] በየጊዜው እያሻቀበ ለመጣው ተጠቃሚ፣ የአካባቢያዊ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት፣ በኢትዮጵያ የተሰየመው የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች ኮሚሽን (ICHREE)፣ በጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም ባቀረበው የማጠቃለያ ሪፖርቱ ከሚከተለው ድምዳሜ ላይ ደርሷል፤ “በኢትዮጵያ፣ በተለይ በኢንተርኔት ላይ የሚወጡ የጥላቻ ንግግሮች በመበራከታቸው የተነሳ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ውጥረት የነገሰ ሲሆን፣ ግለሰቦች እና ቡድኖች የግጭት እና የአመፅ ጥሪ ኢላማ የሆኑበት ሁኔታ ተፈጥሯል።”“የጥላቻ ንግግሮች፣ እንዲሁም በኢንተርኔት ላይ የሚሰነዘሩ የተዛቡ እና ሀሰተኛ መረጃዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ተከሰቶ በነበረው የግጭት ወቅትም ሆነ አሁን ባለንበት ሁኔታ፣ ዘረኝነት እና ብጥብጥ እንዲፈጠር አስተዋፅኦ አድርገዋል ወይም አባብሰዋል። ሆኖም፣ ድርጊቱ ወደፊት እንዳይደገምና ተገቢውንም ትምህርት ለመውሰድ እንዲቻል ገለልተኛ ምርመራ ሊደረግበት ይገባል” ሲል ኢትዮጵያ ውስጥ የተሰየመው የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች አሳስቧል። በዚህ ሪፖርትም የቀረበው፣ ግጭትን በመቀስቀስ ረገድ የሜታን አሉታዊ ተጽዕኖ በተመለከተ፣ የገለልተኛ ምርመራ ወጤትን ነው።

እራሱ ፌስቡክ ውስጥ የተገኙ፣ የፌስቡክ መዛግብት አካል የሆኑ፣ በ2013 ዓ.ም በቀድሞ የሜታ ሰራተኛ የተለቀቁ ተከታታይ ሰነዶች እንደሚያመለክቱት፣ ሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው ግጭት ወቅት፣ በድርጅቱ የሚሰራጩ መልዕክቶች በሀገሪቱ የሚደርሱ የሰብአዊ መብት ጉዳቶችን የማባባስ አደጋ እንደነበራቸው ሜታ እውቀቱ የነበረው ቢሆንም፣ አደጋውን በበቂው ሁኒታ ለመቀነስ ጥረት ሳያደርግ ቀርቷል። በ2013 ዓ.ም የወጣው [የሜታ] የውስጥ ሰነድ፣ ኢትዮጵያን “በከባድ” የብጥብጥ ስጋት ውስጥ ያለች ሀገር በማለት ፈርጇታል፤ ሀገሪቱ ውስጥ እየተሰራጩ ያሉ የአመጽ እና ግጭት ቀስቃሽ መልዕክቶችን በተመለከተ ተገቢውን ምላሽ የመስጠት አቅም ደረጃው ዜሮ ከሶስት እነደነበር ገልጿል። በሌላ ሰነድ ደግሞ፣ አንድ የሜታ ሰራተኛ፣ በ2013 ዓ.ም ሀገሪቱ ውስጥ ከሚካሄደው ምርጫ ጋር በተያያዘ ፣ በኢትዮጵያ “ይዘትን የሚገመግሙ በቂ ባለሞያዎች” እንዳልነበሩት አምኗል። ግጭቱ እየቀጠለ በሄደበት ወቅት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ቡድኖች እና የዲጂታል መብት ባለሙያዎች፣ የፌስቡክ መድረክ በኢትዮጵያ ውስጥ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ ለሚደርሰው የሰብአዊ መብት ረገጣ እና በደል የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያደርግ እንደሚችል ያላቸውን ስጋት ገልፀው ነበር። ይህ ሪፖርት የእነዚህን ወገኖች ስጋት እና ክሶች በመፈተሽ፣ ከ2013 እስከ 2015 ዓ.ም በነበሩት ጊዚያት በትግራይ ተወላጆች ላይ የተፈፀሙ አሰቃቂ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እና ግፎችን አስመልክቶ፣ የሜታ ሚና ምን እንደነበረ የሰብአዊ መብት ትንተና ያደርጋል፤ ከዚህ በተጨማሪም፣ ኢትዮጵያ ለወደፊቱ

**“ለአባቴ የሞት ፍርድ”**

በሰሜን ኢትዮጵያ ለደረሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሜታ ያደረገው አስተዋጽኦ

አምነስቲ ኢንተርናሽናል

ተመሰሳይ እጣ እንዳይገጥማት ጉዳቱን በመከላከል ወይም በመቀነስ ረገድ፣ የሜታ ሃላፊነት እስከምን ድረስ ነው የሚለውን ጉዳይም ይህ ሪፖርት ይዳስሳል፤ ምክንያቱም፣ ምንም እንኳን በኢትዮጵያ መንግስት እና በህወሓት መካከል የሰላም ስምምነት የተደረገ ቢሆንም፣ አካባቢው የግጭት ቀጠና እንደሆነ ቀጥሏል።

በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ውስጥ የምትሰራ እና በሰሜን ኢትዮጵያ ግጭት ወቅት የሜታ 'ሁነኛ አጋር' ፕሮግራም አካል የነበረችው ገሊላ በአጽንኦት እንደተናገረችው፣ በአሰራሩ ላይ አፋጣኝ ማሻሻያ ካልተደረገበት በስተቀር፣ የፌስቡክ መድረክ የሰብአዊ መብት ረገጣን በማባባስ ረገድ፣ የራሱ አሰተዋፅኦ ሊኖረው ይችላል፤ (ገሊላ የምትሰራበት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት፣ ለተመረጡ የሲቪል ማህበራት፣ በመድረኮቹ አማካኝነት ሜታ ስለሚያሰራጫቸው ጎጂ መልዕክቶች፣ ባዘጋጃቸው ቻናሎች አማካኝነት ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ ማህበር መሆኑን ልብ ይሏል)

**“ኢትዮጵያ ውስጥ ለረጅም ጊዜ እንደኖረ ዜጋ፣ ፌስቡክ ማህበረሰቦች ለእርስ በእርስ ግጭት ይበልጥ እንዲጋለጡ እያደረገ ነው ማለት እችላለሁ።”**

ይህ ሪፖርት፣ ሜታ፣ የመልዕክት ይዘትን በየመልኩ በሚፈርጀው አልጎሪዝሙ (content-shaping algorithms) እና መረጃ-በሚያጋብስ (data-hungry) የንግድ ሞዴሉ አማካኝነት፣ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ ለደረሰው ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰት እና ግፍ ስላደረገው አስተዋፅኦ ያትታል ።ሪፖርቱ፣ ሜታ ከሲቪል ማህበረሰብ ተዋናዮች የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ችላ በማለት እና ግጭቱ ከተፈጠረ በኋላም እንኳ፣ ምንም አይነት የማሻሻያ እርምጃዎችን እንዳልወሰደ ያሳያል። እነዚህ ድክመቶች፣ የመልዕክት ይዘትን በየመልኩ ከሚፈርጁ አልጎሪዝሞች ጋር ተዳምረው፣ የተጠቃሚዎችን ተሳትፎ ከፍ በማድረግ ግጭት ቀስቃሽ መልዕከቶች ተጠናክረው እነዲቀጥሉ ምክንያት ሆነዋል፣ ይህም ደግሞ ፌስቡክ የትግራይ ህዝብ እንዲጠላ በሚያበረታቱ መልክቶች እንዲሞላ እና መልዕክቶቹም በማህብረሰቡ ላይ ሁከትን፣ አድልዎን የጥላቻ ስሜትን እንዲያባብሱ አስተዋፅኦ አድርገዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ለደረሰው የሰብአዊ መብት ጥሰት እና ግፍ ሜታ ያደረገው አስተዋፅኦ የታየው፣ በማይናማር በህዳር ወር 2009 ዓ.ም በሮሂንጃዎች ላይ እልቂት ከተፈፀመ ከሶስት አመታት በኋላ ነበር፤ በዚህ እልቂትም፣ የፌስቡክ ድርሻ ከፍተኛ ነበር። ሜታ አሁንም ለሰብአዊ መብት ጉዳቱ አስተዋፅኦ እያደረገ ለመሆኑ ተጨማሪ መረጃ የሚሆነው በወረራ-አከል የቢዝነስ ሞዴሉ አማካኝነት የንግድ ማስታወቂያዎች ላይ በማነጣጠር ጎጂ የሆኑ የመልዕክ ይዘቶችን ማባባሱ ነው። ማባሪያ በሌለው የተጨማሪ መረጃ ፍለጋ ስልት የሚሰሩት የሜታ አልጎሪዝም ስርዓቶች፣ በጣም ግጭት ቀስቃሽ፣ ከፋፋይ እና ጎጂ ለሆኑ ይዘቶች ቅድሚያ ይሰጣሉ፤ ይህን የሚያደረጉት የተጠቃሚዎችን ተሳተፎ ከፍ ለማድረግ ሲባል ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ፣ በሀምሌ ወር 2013 ዓ.ም የትግራይ ኃይሎችን “አረም” እና “ካንሰር” በማለት ያስተላለፉት የፌስቡክ መልዕክት፣ በወቅቱ ፌስቡክ ላይ ተጋግሎ በነበረው በትግራይ ማህበረሰብ ላይ ያነጣጠረ ጎጂ መልዕክት ዓይነተኛ ምሳሌ ነው። እስከ ጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም ድረስ፣ መልዕክቱ በፌስቡክ ላይ ተለጥፎ ይታያል። ልጥፉ፣ ከ8,000 ጊዜ በላይ ተጋርቷል፤ በሺዎች የሚቆጠሩ አስተያየቶችንም አግኝቷል፤ ከእነዚህ አስተያያቶች መካከል፣ “ጠላት ይውደም’!” “ኢትዮጵያ ትቅደም!" የሚሉ ይገኙበታል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራሳቸው በፌስቡክ ገፅ ላይ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ ጥላቻና አድሎአዊ ይዘትን ሲለጥፉ መቆየታቸው፣ ለስርጭቱ ትልቅ አስተዋጽኦ ነበረው። ሜታ፣ የአንድን ፖለቲከኛ ንግግር ተገቢ መሆን አለመሆን ላይ አስተያየት መስጠት እንደማይፈልግ ቀድሞ አቋሙን ያሳወቀ ቢሆንም፣ ሁከትን ሊቀሰቅሱ የሚችሉ መልዕክቶች የህዝብን የመሳተፍ ፍላጎት ከማነሳሳት ይልቅ የደህንነት ስጋት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያምናል።

የሰሜን ኢትዮጵያ ግጭት ከመቀስቀሱ በፊት እና በግጭቱ ወቅትም፣ የሲቪል ማህበረሰብ ተሟጋቾች እና የዲጂታል መብት ባለሙያዎች፣ እያንዣበቡ ስለነበሩት አደጋዎች መፍትሄ እንዲፈልግ ሜታን ደጋግመው ተማጽነዋል። ይህ ሪፖርት፣ የራሱን የሜታን የቁጥጥር ቦርድ ጨምሮ፣ከ2013 እሰከ 2015 ዓ.ም ባሉት ጊዚያት፣ በተለያዩ ወገኖች ከሜታ ጋር የተደረጉ ግንኙነቶች እና የተሰጡ የመፈትሄ ሀሳቦችን ሰንዷል። ከነዚህ ጥረቶች በተጨማሪ፣ በማይናማር በሮሂጃዎች ላይ ለደረሰው ከባድ ሁከት፣ የሜታ አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑ ቢታወቅም፣ ድርጀቱ ለተሰጡት ማስጠንቀቂያዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ብሏል ወይም በበቂ ሁኔታ እውቅና አልሰጣቸውም ማለት ይቻላል።

በተጨማሪም፣ የሰሜን ኢትዮጵያው ግጭት ከመቀሰቀሱ በፊት እና በግጭቱ ወቅትም፣ ሜታ ኢትዮድያ ውስጥ የሚሰራጩ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ ያነጣጠሩ መልዕክቶችን ለመቆጣጠር ወይንም ከፌስቡክ ላይ ለማውረድ የሚያስችል በቂ መዋዕለ ንዋይ ሙሉ ለሙሉ አለመመደቡ የችግሩ ዋናው ምክንያት ነበረ። ኢትዮጵያ ውስጥ 85 ቋንቋዎች የሚነገሩ ቢሆንም፣ ሜታ የመልዕክቶችን ይዘት መቆጣጠር የቻለው በሶስት ቋንቋዎች ብቻ ነበር። ይህም፣ ኩባንያው እንግሊዝኛ ተናጋሪ ባልሆኑ፣ በዓለም ላይ ባሉ አብላጫ ሀገሮች ውስጥ በይዘት ማስተካከያ ላይ በበቂ ሁኔታ መዋለ-ንዋይ መመደብ ያለመቻሉ ዋና ማሳያ ነው። በኢትዮጵያ የተሰየመው የዓለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ኤክስፐርቶች ኮሚሽን የጥናት ግኝትም፣ የፌስቡክ መድረክ፣ "ምላሽ ለመስጠት በጣም የሚንቀራፈፍ፣ በቂ የሰው ኃይል የሌለው፣ የቋንቋ ችሎታዎቹ በቂ ያልሆኑ እና የፋይናንስ አቅም እጥረት ያለበት" መሆኑን አሳስቧል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ሊከሰት ስለሚችለው የጅምላ ብጥብጥ ሜታ አስተዋፅኦ ሊኖረው ይችላል የሚለው ስጋት፣ በግንቦት 2012 ዓ.ም በሰሜን ኢትዮጵያ ከተቀሰቀሰው ጦርነት በፊት በግልፅ ተለይቶ መታወቅ ነበረበት። በሰኔ ወር 2012 ዓ.ም የታዋቂው የኦሮሞ ዘፋኝ እና አክቲቪስት ሃጫሉ ሁንዴሳ ግድያን ተከተሎ፣ ፌስቡክ፣ ሁከትን እና ጥላቻን በሚያበረታቱ፣ ብጥብጥን በሚቀሰቅሱ፣ የ“በቀል” ጥሪዎች

እና ወደ አረመኔያዊ የህዝብ ብጥብጥ በሚያመሩ መልዕክቶች ተጥለቅልቆ ነበር። ይህንን ክስተት ተከተሎ፣ ሜታ፣ የማህበረሰብ[መስተጋብር] መመሪያውን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አማርኛ ተርጎሞ አቀረበ። ይሁን እንጂ፣ ይህ እርምጃ፣ በፌስቡክ አማካኝነት ተደቅነው ከነበሩ አደጋዎች አንፃር ሲታይ፣ ችግሩን በበቂ ሁኔታ ለመግታት መወሰድ ከሚገባቸው እርምጃዎች በጣም አነስተኛው እርምጃ ነበር።

የሲቪል ማኅበራት፣ የፌስቡክ ፕላትፎርም ኢትዮጵያ ውስጥ ሊያስከትል ስለሚችለው የብጥብጥ አደጋ ለሜታ ለማጠቆም ጥረት አድርገዋል። በሰኔ ወር 2012 ዓ.ም፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ከመጀመሩ አራት ወራት ቀደም ብሎ፣ የዲጂታል መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ በኢትዮጵያ በፌስቡክ ስለሚሰራጩ ጎጂ ይዘት ያላቸው መልዕክቶች አስመልክቶ ለሜታ የላኩት ደብዳቤ፣ “[የፊስቡከ መልዕክቶቹ] ወደ አካላዊ ግጭት፣ ወደ ብጥብጥ እና ወደአናሳ ቡድኖች መድልኦ ሊያመሩ ይችላሉ” የሚል ማስጠንቀቂያ ነበረው፤ ከዚህ በተጨማሪ፣ ደብዳቤው፣ ጉዳትን ለመከላከል የሚረዱ ሌሎች ምክረ-ሀሳቦች ነበሩት፤ ከእነዚህ መካከል፣ ግጭት ቀስቃሽ መልዕክቶችን የሚያጎሉ አልጎሪሞችን ማስቆም፣ በአንዳንድ አሰራሮች ላይ ጊዜያዊ ለውጦች ማድረግን እና ኩባንያው ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚያከናውናቸው አንዳንድ ተግባራት የሰብአዊ መብት ተፅዕኖ ግምገማ እንዲያደረግ የሚጠይቁ ምክረ-ሀሳቦች ተካተውበታል።

ምላሾችን በመሰጠት ረገድ የሜታን ቀርፋፋነት እና ኩባንያው ለሀገር በቀል እውቀት የሚሰጠውን አነስተኛ ግምት አስመልከቶ፣ ገሊላ እንዲህ ትላለች፤

> **“ለነገሮች ምላሽ በመስጠት ረገድ፣ በጣም ቀርፋፎች ናቸው። የሚነገራቸው ነገር አያስጨንቃቸውም – የእነሱ [የነገሮች] መመዘኛ መስፈርቶች፣ መሬት ላይ እየተካሄደ ካለው ሁኔታ ጋር በእጅጉ የተራራቀ መስሎ ይሰማኛል። የአካባቢው ሰው ስትሆን የትኛው ነገር፣ የትኛውን ነገር ሊቀሰቅሰው እንደሚችል ይገባሃል፤ ከፖሊሲያቸው አንፃር መልዕክቱ የጥላቻ ንግግር መሆን አለመሆኑን ሜታዎች ላይለዩት ይችላሉ፤ ምዕራቡ ዓለም ካለው ቢሯቸው ቁጭ ብለው የራሳቸውን ግንዛቤ ሊወሰዱ ይችላሉ፤ ቦታው ላይ ስትሆን ግን የትኛው መልዕክት የጥላቻ ንግግር እንደሆነ ይገባኻል።”**

ሜታ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እያስከተለው ስላለው ችግር፣ በተደጋጋሚ በቂ ሀላፊነትን ሳይወስድ ቀርቷል። የካቲት 7 ቀን 2013 ዓ.ም በተላለፈ ውሳኔ፣ የፌስቡክ ቁጥጥር ቦርድ፣ ያልተረጋገጡ አሉባልታዎችን እና ጥላቻን በሀገሪቱ ውስጥ በማሰራጨት ረገድ፣ የፌስቡክ ሚና ምን ያህል እንደነበረ ሙሉ ግምገማ እንዲያካሂድ ምክረ-ሀሳብ አቅርቧል። ይህ ምከረሀሳብ የተሰጠው፣ ኢትዮጵያ ወስጥ ምርጫ ከመካሄዱ ቀደም ብሎ ሜታ ባካሄደው የ2013 ዓ.ም የሰብአዊ መብት ተፅእኖ ግምገማ ነው። በጥር ወር 2013 ዓ.ም፣ ሜታ በኢትዮጵያ ውሰጥ ያልተረጋገጡ አሉባልታዎችን እና የጥላቻ ሰርጭትን በተመለከተ የሰብአዊ መብት ተፅእኖ “ግምገማ አዋጭነት” እንደሚያደረግ ምላሽ ሰጥቶ ነበር። ይሁን እንጂ፣ እስከ ጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም ድረስ፣ እንደዚህ ዓይነት ግምገማ እየተደረገ ስለመሆኑ ወይም የግምገማው ሂደት ስለመጀመሩ የሚያሳይ አንዳችም ማስረጃ የለም።

በታህሳስ ወር 2010 ዓ.ም፣ በማይናማር የሮሂንጃ ህዝብ ላይ በተፈጸመው የዘር ማጽዳት ወንጀል ውስጥ ከፍተኛ ሚና ከተጨወተ ከጥቂት ወራት በኋላ፣ ሜታ "ትርጉም ያለው ማህበራዊ መስተጋብር" (MSI) ብሎ የሰየመውን የኒውስ ፊድ አልጎሪዝም በአዲስ ሜትሪክ ዙሪያ ቀየረ። ይህ ለውጥ፣ እያሽቆለቆለ የነበረውን የፌስቡክ ተጠቃሚዎች ተሳትፎ ለማሻሻል ያለመ ቢሆንም፣ ዋና ስራ አስፈፃሚው ማርክ ዙከርበርግ ግን ለውጡ፣“ፌስቡክን ለማስተካከል የተደረገ ጥረት” አስመስለው አቅርበውታል። የዚህ ሪፖረት ግኝት ግን፣ "ትርጉም ያለው ማህበራዊ መስተጋብር" በሌላ ስም የቀረበ የተጠቃሚዎችን ተሳተፎ የሚጨምር ስልት መሆኑን እና በተለይም በግጭት በተጎዱ አካባቢዎች ከፍተኛ ስጋትን እንደሚያጭር ያሳያል። ቀመሩ (ሜትሪኩ) አስተያየቶችንም ሆነ የተጠቃሚዎችን መስተጋብር ያበረታታል፤ ነገር ግን፣ ቀመሩ የሚሰራው በተሳትፎ ላይ ተመስርቶ ደረጃን በማውጣት ነው፤ የሜታ የውስጥ ሰነዶችም "ትርጉም ያለው ማህበራዊ መስተጋብር" (MSI)፣ የግጭት ቀስቃሽ እና የጎጂ አልጎሪዝምን የማጉላት መጠንን ከፍ እንደሚያደርግ ይጠቁማሉ።

የፌስቡክ ሰነዶቹ የሜታ ዋና ስራ አስፈፃሚ ማርክ ዙከርበርግ የተሰጡትን የመፍትሄ እርምጃዎች ተግባር ላይ እንዳይዉሉ ለማስቆም በግል ጣልቃ መግባታቸውን የሚጠቁሙ መረጃዎችን ይዘዋል። ይህንንም ያደረጉት፣ የመፍትሄ እርምጃዎቹ፣"ትርጉም ያለው ማህበራዊ መስተጋብር” ላይ ሊያስከትሉ የሚችሉት አሉታዊ ተፅዕኖዎች ስላሉትና ብሎም በየፌስቡክን ትርፋማነት ላይ ስጋት ስለሚጥል ነው። የሰነዱ ፀሀፊ፣ ‘ቀለል ያሉ ድርጊቶች’ (‘soft actions’) የሚለውን ፅንሰ-ሀሳብ (‘ቀለል ያሉ ድረጊቶች’ የሚለው ፅንሰ-ሀሳብ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የአደጋ ስጋት በተጋረጠባቸው ሀገራት የመልዕክት ይዘቶችን ለማስወገድ ሜታ ሊጠቀምባቸው የሚችላቸው ሰፊ አማራጮች የያዘ ጥቅል ቃል መሆኑን ልብ ይሏል) ባብራሩበት ጽሁፋቸው እንዲህ ይላሉ፤ “ማርክ ነገሩን በጥልቀት መስራት አለባችሁ ብሎ አያምንም... "ትርጉም ያለው ማህበራዊ መስተጋብር” (MSI) ምንም ጥቅም አይሰጠንም ብለን ብናስብ ኖሮ፣ ጥቅም ላይ አናውለውም ነበር”። በዚህ ሰነድ ውስጥ፣ ኢትዮጵያ ለአደጋ የተጋለጠች ሀገር በመሆኗ፣ ‘ቀለል ያሉ ድረጊቶች’ በጊዚያዊነት የሚሞከሩባት ሀገር ተብላ ተጠቅሳለች።

የሜታን የመልዕክት ይዘትን የማጋነን ነገር በተመለከተ በ2013 ዓ.ም ለኮንግረስ ምክርቤቱ በሰጠችው ምስክርነት፣ የፌስቡክ መረጃ ጠቋሚዋ (whistleblower) ፍራንሲስ ሃውገን፣ ኢትዮጵያን በመጥቀስ እንዲህ ትላለች፤

**“[ሜታ] የተጠቃሚን ተሳትፎን ማዕከል ያደረገ የደረጃ አወጣጥ አሰራር በታማኝነት እና ደህንነትን በሚጠብቁ ስርዓቶች እስካልታገዘ ድረስ፣ አደገኛ መሆኑን ያውቃል፤ በግልጽም ተናግሮታል። ነገር ግን፣ እነዚህ ስርዓቶች በአብዛኛዎቹ በዓለም ላይ ላሉ ቋንቋዎች አልተዘረጉም። እናም ይሕ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ እንደታየው [አይነት] የጎሳ ግጭት ምክንያት እየሆነ ያለው።”**

ሁሉም ኩባንያዎች በዓለም ውስጥ በሚሰሩበት በማንኛውም ቦታ እና በሚሰሩበት ጊዜ ሁሉ ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ሀላፊነት አለባቸው። ይህንን ሀላፊነት ለመወጣት፣ ኩባንያዎች በሰብአዊ መብቶች ላይ የሚያደርሱትን ተፅእኖ ለመለየት፣ ለመከላከል፣ ለማቃለል እና ተጠያቂ ለመሆን ቀጣይነት ያለውና ችግሩ ከመከሰቱ በፊት የሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር ትጋት ( due diligence ) ማሳየት አለባቸው። እንደ ሜታ ላሉ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች፣ ተገቢ ትጋት የእነርሱ የንግድ ሞዴል እና የንድፍ ውሳኔዎች የሰብአዊ መብት አደጋዎችን የሚፈጥሩ ወይም የሚያባብሱበትን ሁኔታዎችን ማካተት አለበት።

በ2013 ዓ.ም፣ የሰሜን ኢትዮጵያ ግጭት ከመከሰቱ በፊትም ሆነ የሜታ የራሱ ቁጥጥር ቦርድ በሀገሪቱ ውስጥ የሰብአዊ መብት ተፅዕኖ ግምገማ እንዲደረግ ሀሳብ ካቀረበለት በኋላ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያከናውናቸውን ተግባራት በተመለከተ፣ ሜታ ተገቢውን የሰብአዊ መብት ትጋት አላደረገም። ይህ ትንታኔ እንደሚያሳየው፣ ሜታ ግጭት በተከሰተባቸው ሁኔታዎች፣ ለከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እና በደሎች አስተዋፅኦ እንዳለው የማያጠራጥር ነው።

ሀምሌ 11 ቀን 2015 ዓ.ም፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ለሜታ በጻፈው ደብዳቤ፣ ኩባንያው ኢትዮጵያ ውስጥ፣ በሰሜኑ ክፍል ግጭት ከመከሰቱ በፊትም ሆነ ከተከሰተ በኋላ፣ በፌስቡክ መድረክ ላይ የሰብአዊ መብት ረገጣ እንዳይካሄድ ምን አይነት የመከላከያ እርምጃዎችን እንደወሰደ ጠይቋል። ከ2013 ዓ.ም አንስቶ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበራቸውን የትጋት አካሄድ እና የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ በመዘርዘር ሜታ ምላሽ ሰጥቷል። ይሁን እንጂ፣ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ስለተያዘ፣ ሁሉንም የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ጥያቄዎች መመለስ እንደማይችል አስገንዝቧል። በጥቅምት ወር 2015 ዓ.ም፣ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ እዚህ ሪፖርት ውሰጥ ስለተካተቱ ውንጃላወች ለሜታ እንደገና ሌላ ደብዳቤ ፃፈለት። ሜታም፣ ለተጻፈለት ደብዳቤ በሰጠው መልስ፣ በሪፖርቱ ግኝቶች እንደማይስማማ ገልጾ፣ጉዳዩ በፍርድ ቤት ከመቋጨቱ በፊት ተጨማሪ ማብራሪያ ለመስጠት እንደሚቸገር አሳውቋል።

እስከ ዛሬ ድረስ፣ የሜታ አሰራሮች በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚፈጥሩት አደጋዎች በበቂ ሁኔታ መፍትሄ መስጠት ሳይችል ቀርቷል። ያም ሆኖ፣ ኩባንያው ወደፊት ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በተገቢው መንግድ ለመቀነስ የሚያስችለውን ተገቢ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት፣ ከምንጊዜውም በላይ አስቸኳይ እየሆነ መጥቷል። በአሁኑ ወቅት፣ በአማራ ክልል ቀውስ እየተፈጠረ እና የብሔር ግጭት በመላው ኢትዮጵያ እያቆጠቆጠ ያለበት ሁኔታ አለ። ይህ ሁኔታ፣ በሀገሪቱ ውስጥ እየተደረገ ካለው የቴሌኮሙኒኬሽን ኔትወርክ መስፋፊያ ስራ ጋር ተዳምሮ፣ የፌስቡክ ፕላትፎርም፣ አሁንም የጥላቻ፣ የጥቃት እና የመድልዎ ማስተላለፍያ ሆኖ አንዲያገለግል ሁኔታዎች ተመቻችተውለታል ማለት ነው።

በአሁኑ ጊዜ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ለተፈጸሙ የሰብአዊ መብት ረገጣዎች አስተዋጾ አድርጓል በሚል፣ ሜታ፣ ኬንያ ውስጥ የፍትሐ ብሔር ክስ ቀርቦበታል። ክሱን የመሰረቱት፣ ሁለት ተጎጂ ግለሰቦች (አብርሃም ማዕረግ እና ፍስሃ ተክሌ) እንዲሁም በኬንያ የሚገኝ የካቲባ ኢንስቲትዩት የተሰኘ አንድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ናቸው። ጥያቄያቸውም፣ ሜታ፣ የፌስቡከ አልጎሪዝሞች፣ ጎጂ መልዕክቶችን ተጠቃሚዎች እንዲያዩ ከማበረታት እንዲታቀብ ማድረግ እና እስካሁን ላደረሰው ጉዳትም የ1.6 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተጎጂዎች ፈንድ እንዲፈጥር ማስገደድ ነው።

በዚህ ዘገባ ውስጥ በዝርዝር እንደተገለፀው፣ ሜየተባበሩት መንግስታት የንግድ እና የሰብአዊ መብቶች መመሪያዎች በሚያዙት መሰረት፣ ሜታ፣ የሰብአዊ መብትን የመጠበቅ ሀላፊነቱን ባለመወጣቱ፣ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል። ጉዳቱን ይበልጥ የከፋ የሚያደረገው ደግሞ፣ ኩባንያው ማይናማር ውስጥ ለደረሰው ከባድ የሰብአዊ መብት ረገጣ አስተዋፅኦ ማድረጉ ከተረጋገጠ በኋላም፣ ተመሳሳይ የአሰራር ግድፈቶቹን ኢትዮጵያ ውስጥም መድገሙ ነው። የሜታ የንግድ አሰራሮች፣ ሰብአዊ መብቶች ላይ፣ በተለይ የግጭት ሰለባ በሆኑ አካባቢዎች፣ ከፍተኛ አደጋ እንደሚያስከትሉ ከዚህ የበለጠ ፍንትው ብሎ ሊታይ አይችልም። በሌሎች ሀገራትም፣ ለእነዚህ አይነት ጉዳቶች መባባስ በድጋሚ አስተዋጽኦ እንደማያደርግ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አስቸኳይና መጠነ ሰፊ ማሻሻያዎችን ማድረግ ያስፈልጋል፤ ይህም፣ በዋናነት፣ የተጠቃሚዎችን ተሳትፎ መሰረት ያደረገ የንግድ ስራ ሞዴሉን ለመቀየር ሜታ ቁርጠኛ እንዲሆን ማድረግን እና የሰብአዊ መብት ጉዳቶች ወደፊት እንዳይደገሙ ማረጋገጥን ይጨምራል።

ሜታ ኢትዮጵያ ውስጥ እያሳየው ያለው ተደጋጋሚ የአሰራር ችግር፣ ኩባንያው፣ አሁንም አሉታዊ የሆኑ የሰብአዊ መብት ተጽዕኖ ምንጮችን ነቅሶ ማውጣት አለመቻሉን ያመለክታል። የሜታ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተደጋጋሚ ምክንያት የመሆኑ ምንጭ እየተከተለው ያለው “ሰዎችን እግር-በእግር የሚከታተል የንግድ ሞዴል” (surveillance-based business model)ነው፤ ይህ ሌሎች በርካታ ትላልቅ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችም የሚጠቀሙበት አይነት ሞዴል ነው። እነዚህ ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉት፣ በጠንካራ እና ትርጉም ባለው የመንግስት ደንብ እና ቁጥጥር ብቻ ነው። የትላልቅ ኩባንያዎችን የንግድ ሞዴል አሰራር ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመቆጣጠር የሚያስችል ህግ በማውጣት እና ህጉንም ተፈጻሚ በማድረግ፣ መንግታት የሰብአዊ መብቶችን የማክበር ግዴታቸውን መወጣት አለባቸው።

## **“ለአባቴ የሞት ፍርድ”**

በሰሜን ኢትዮጵያ ለደረሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሜታ ያደረገው አስተዋጽኦ

አምነስቲ ኢንተርናሽናል

በከባድ ሀዘን ላይ ያለው የፕሮፌሰር ማዕረግ አማረ ልጅ፣ አብርሃም ማዕረግ፣ ኩባንያው በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያደርሰው አደጋ ባስቸኳይ ትምህርት ሊወስድ እንደሚገባ አስምሮበት፣ በሜታ ላይ የፍትሐ ብሔር ክስ ለመመሥረት የተነሳሳበትን ምክነያት ሲገልጽ፣ "**የበርካቶችን ህይወት ልንታደግ እንችላለን**" ብሏል።

**"ለአባቴ የሞት ፍርድ"**

በሰሜን ኢትዮጵያ ለደረሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሜታ ያደረገው አስተዋጽኦ

አምነስቲ ኢንተርናሽናል

# 2. ማጠቃለያ እና ምክረ ሃሳቦች

**"ደግመን ደጋግመን የምንሰማው ያንኑ አንድ ታሪክ ነው። የሚለወጥ ነገር የለም። ማይናማር ውሰጥም፣ ሰዎች ተመሳሳይ ነገር ተናግረው ነበር። ሌላ ቦታም ተመሳሳይ ነገር ይከሰታል።**“[1]

ትምኒት ገብሩ

## ማጠቃለያ

ይህ ዘገባ፣ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ የተፈጸሙ ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በተመለከተ፣ ሜታ የተጫወተውን ሚና በጥልቀት በመመርመር፣ ኩባንያው ለእነዚህ ጉዳቶች አስተዋፅኦ እንዳደረገ እና በዚህም ለተጎዱ ግለሰቦች መፍትሄ የመስጠት እና ተጨማሪ አፋጣኝ እርምጃዎችን የመውሰድ ተዛማጅ ሀላፊነት እንዳለበት አረጋግጧል በመሆኑም፣ ኩባንያው በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች በዓለማችን ውስጥ በሚገኙ የግጭት ሰለባ በሆኑ አካባቢዎች የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል።

በከፍተኛ ደረጃ ለአደጋ በተጋለጡ እና የግጭት ሰለባ በሆኑ አካባቢዎች እንደሚሰራ እንደ አንድ ዓለም አቀፋዊ ኩባንያ፣ ሜታ እየተከተለ ያለው የአሰራር ስልት፣ በአናሳ ብሔረሰቦች እና ሀይማኖቶች እንዲሁም በሌሎች የአለማችን ክፍሎች በሚገኙ ኣካባቢዎች ዘንድ፣ ጥላችን ሊያበረታታ እና ሁከትን ሊያጭር ይችላል። ይህ የማስጠንቀቂያ ደወል፣ በበርካታ አውዶች ለአመታት ሲሰማ ቆይቷል። ሜታ፣ በማይናማር አስከትሎት የነበረውን ጉዳት ኢትዮጵያን ጨምሮ በሌሎች ሀገራት እየደገመው መሆኑን፣ የመረጃ አነፍናፊዋ፣ ፍራንሲስ ሃውገን፣ ደጋግማ አስጠንቅቃለች፤

> **"በማይናማር ያየነው እና አሁን ደግም ኢትዮጵያ ውስጥ እያየነው ያለው ነገር፣ ማንም እስከ መጨረሻው ሊያነበው የማይፈልገውን የአንድ የሰቆቃ ታሪክ የመጀመሪያዎቹን ምዕራፎች ነው።"**[2]

የእነዚህ አደጋዎች እና ጉዳቶች ዋነኛ ምክንያት፣ ሜታ እየተጠቀመበት ያለው የመልዕክት ይዘትን በየመልኩ የሚፈርጀው አልጎሪዝም መሆኑን ሃውገን በተለየ አስምራበታለች።[3] እንደ ህንድ እና ስሪላንካ ባሉ ሌሎች ሀገራትም፣ ሁከትን፣ ጥላቻን እና /ዘረኝነትን

[1] አምነሰቲ ኢነተርናሽናል ከትምኒት ገበሩ ጋር ሰኔ 30 2015 ዓ.ም ካደረገው የቪዲዮ ቃለ-መጠይቅ የተወሰደ

[2] የፌስቡክ መረጃ መንታፊዋ፣ ፍራንሲስ ሃውገን፥ ህፃናትንና ማህበራዊ-ሚዲያን አስመልክቶ ምስክርነት፤ የምከርቤቱ ውይይት ሙሉ ቃል https://www.rev.com/blog/transcripts/facebook-whistleblower-frances-haugen-testifies-on-children-social-media-use-full-senate-hearing-transcript

[3] ጋርዲያን፥ ’የፌስቡክ ሚና በማይናማር እና በኢትዮጵያ በአዲስ እይታ፥ ሰኔ 30፥ 2013 ዓ.ም፥ https://www.theguardian.com/technology/2021/oct/07/facebooks-role-in-myanmar-and-ethiopia-under-new-scrutiny

የሚያበረታቱ/የሚያባብሱ ቅስቀሳዎች መስፋፋት የመልዕክቶች ይዘትን በየመልኩ ከሚፈርጀው የፌስቡክ ፕላትፎረም አልጎሪዝም ጋር የተቆራኘ ነው።[4]

ማሕበራዊ ጽንፈኝነት፣ በሀገሪቱ ለአስርተ አመታት ሰፍኖ እና በትግራይ ማህበረሰብ ላይም ሰብአዊነት የጎደላቸው የፖለቲካ ንግግሮች ሲቃጡ ተስተውሏል። ይህ ሁኔታ፣ ተሳትፎን መሰረት ያደረገው የሜታ የንግድ ሞዴል፣ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ የሚያደርሰውን ጥላቻ፣ ጥቃት እና ዘረኝነት እየተለመደ እንዲመጣ አድርጎታል። ተሳትፎን ያማከሉ የኩባንያው አልጎሪዝሞች፣ ጎጂ መልዕክትን ይበልጥ ያገዘፉ ሲሆን፣ “ትርጉም ያለው ማህበራዊ መስተጋብር”(MSI) የተሰኘው ሜትሪክም ብዙ አስተያየቶች እንዲለጠፉ አበረታቷል።በተጠቃሚዎች ተሳትፎ ላይ ያማከሉ የኩባንያው አልጎሪዝሞች ጎጂ ይዘት ያላቸውን መልዕክቶች የሚያገዝፉ እና የሚያበረታቱ ነበሩ፤ ይህም በፊናው፣ የትግራይ ማህበረሰብን ከሰውነት ደረጃ ለማውረድ በሚደረገው ያላሰለሰ ዘመቻ የበኩሉን አስተዋፅዖ አድርጓል። ያም ሆኖ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚደርሰው የጅምላ ብጥብጥ ሊያበረክተው ስለሚችለው ጉዳት ከሲቪል ማህበረሰቡ እና ከራሱ ሰራተኞችም ሳይቀር በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ ቢሰጠውም ለማስጥንቀቂያው ቁብ ሳይሰጠው ቀርቷል። ሜታ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ የሰራው ስህተት ያስከተለው ውጤት ማይናማር ላይ ካሳየው ግዴለሽነት ጋር ተመሳሳይነት ነበረው፤ ቀድሞውንም በጎሳ ግጭት እየተናጠ በነበረው ማህበራዊ ግንኙነት ላይ ነዳጅ በማርከፍከፍ፣ የኋላ ኋላ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ ለተፈፀመው አስከፊ የሰብአዊ መብት ረገጣ የራሱን አስተዋፅኦ አድርጓል።

በተመሳሳይ መልኩ፣ የማይናማር ወታደሮች በ2009 ዓም፣ በራኪን ግዛት በፈፀሙት ጭፍጨፋ፣ ሮሂንጃዎች ላይ ላደረሱት ከባድ የሰብአዊ መብት ረገጣ የሜታ አስተዋጽኦ እንዳለበት አምነስቲ ኢንተርናሽናል በ2012 ዓ.ም ያካሄደው ጥናት ያሳያል።[5] እንደ አምነስቲ ኢንተርናሽናል ትንታኔ፣ ሜታ፣ማይናማር ውስጥ የሚጠበቅብትን ሰብአዊ መብቶችን የማክበር ኃላፊነት እንዳልተወጣ ማሳያዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤ በፌስቡክ ፕላትፎርም አልጎሪዝሞች አማካኝነት ፀረ-ሮሂንጃ ጥላቻን በማግዘፍ ሁከትና ግጭት እንዲቀሰቀስ የተጫወተው ሚና፣ የልጥፎችን ይዘት የሚቆጣጠር የበርማ ቋንቋ ተናጋሪ አለመኖር፣ አልጎሪዝሞቹ ጉዳት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ሜታ ቀድሞ የነበረው እውቀት እና ከጭፍጨፋው በፊትና ጭፍጨፋው ወቅት ከሲቪል ማህበረሰብ ተዋናዮች የሚደርሱትን ማስጠንቀቂያዎችን ችላ ማለቱ[6]።

ጋዜጠኛ ዘካርያስ ዘላለም፣ በሮሂንጃዎችና በኢትዮጵያዊ የፌስቡክ ተጠቃሚዎች መካከል ያለውን የገጠመኝ ንፅፅር በተመለከተ የሚከተለውን አስተያየት ሰጥቷል፤

> **"ከሮሂንጃዎች እና ከኢትዮጵያውያን በባሰ ችግሩን የቀመሰ ያለ አይመስለኝም፤ በማህበራዊ ሚዲያ የተነሳ፣ ነገሮች የቱን ያህል አሰቃቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ ለተማራማሪዎች ለማሳየት ጥምረት የሚፈጥሩ ይመስለኛል"**።[7]

ሜታ፣ ለከባድ የሰብአዊ መብት ረገጣ የበኩሉን አስተዋፅኦ ማበርከቱ በ2009 ዓ.ም፣ በሮሂንጃዎች ላይ ከተፈፀመ ጭፍጨፋ ሶስት ዓመታት በኋላ በተከሰተ ሌላ ግጭት፣ ከባድ የሰብአዊ መብት ረገጣ እንደገና አስተዋፅኦ ማድረጉ፣የግጭት ሰላባ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ትጋትን የማሳየት እና ተገቢና ውጤታማ የመፍትሄ እርምጃዎችን የመውሰድ ፍላጎቱ ላይ ከባድ ያለ ጥያቄ ያስነሳል። ከራሱ የቁጥጥር ቦርድ የሚሰጡትን ምክረ-ሀሳቦች ችላ በማለት፣ ኩባንያው በኢትዮጵያ በጥላቻ ስርጭት እና ከኢንተርኔት ውጭ በሚከሰት ሁከት ላይ ያተኮረ የሰብአዊ መብት ተፅዕኖ ግምገማ አለማድረጉ እና አለማሳተሙ የሚያሳስብና በተለይ ግልፅነትን ለማስወገድ እና ከተጠያቂነት ለመሸሽ ሌላ ሙከራ እያደረገ ስለመሆኑ አመላካች ነው ።

ምንም እንኳን በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ወቅት፣ ኩባንያው በኢትዮጵያ የመልዕቶችን ይዘት ቁጥጥር፣ የቋንቋ አመዳደብን እና በተደጋጋሚ የሚጋሩ መልዕክቶችን ቁጥር የመቀነስ አይነት የማሻሻያ እርምጃዎች ወስዶ የነበረ ቢሆንም፣ ማሻሻያዎቹ ለብዙዎቹ የችግሩ ሰለባዎች እጅግ የዘገዩ እና ሊያደርሱት የሚችሉትን አሉታዊ የሰብአዊ መብት ተጽፅኖዎች በበቂ ሁኔታ ለመቀነስ ከሚጠበቅባቸው ደረጃ አንፃር ሲታዩ፣ ማሻሻያዎቹ ከበቂ በታች ነበሩ። ከዚህ በተጨማሪም፣ እርምጃዎቹ የሚሸፍኗቸው ጉዳዮች እጅግ ውስኖች በመሆናቸው፣ ችግሮቹ እንዳይደገሙ ዋስትና መስጠት አይችሉም፤ ምክንያቱም፣ ሜታ ለሰብአዊ መብቶች ስጋት መንስኤ እንዲሆን ያደረገውን የመረጃ-ማጋበስ አሰራር የማይመለከቱ በመሆናቸው ነው።

የዚህ ጥናት ግኝቶች፣ በሜታ የንግድ ሞዴል ላይ ምን ያህል አፋጣኝ ለውጦች ሊደረጉ እንደሚገባ በግልጽ ያሳያሉ፤ ኩባንያው በኢትዮጵያም ሆነ በሌሎች የግጭት ሰለባ በሆኑ የዓለም ዙሪያ አካባቢዎች ለሚፈጸሙ አስከፊ የሰብአዊ መብት ረገጣዎች የበኩሉን

---

4 ታይም፥‘ማይናማር ውስጥ ሁከትን ለማባበስ፤ ጥላቻ ንግግር ላይ ያተኮሩ አንድ አዲስ ዘገባ ከስህተቱ በበቂ ሀኔታ አሳየ’፥ ጥቀምት 18 2012፤ https://time.com/5712366/facebook-hate-speech-violence/ ፤ መጣጥፍ አንድ፥ “ሲራላንካ ውሰጥ በሰባአዊ መብቶች ላይ የየፌስቡክ ተፅዕኖ ላይ የተረግ ግምገማ”፥ 2010፥

https://about.fb.com/wp-content/uploads/2020/05/Sri-Lanka-HRIA-Executive-Summary-v82.pdf

5 *አምነስቲ ኢነተርናሽናል፥ ማህበራዊ ጭፍጨፋ፤ ሜታ እና ሮሂንጃዎች መፍትሄ የማግኘት መብት፥* (ኢንዴክስ፤ ASA 16/5933/2022), መስከረም 19 2015 ዓም, https://www.amnesty.org/en/documents/asa16/5933/2022/en/

6 *አምነስቲ ኢነተርናሽናል፥ ማህበራዊው ጭፍጨፋ፤ ሜታ እና ሮሂንጃዎች መፍትሄ የማግኘት መብት፥* (ኢንዴክስ፤ ASA 16/5933/2022), መስከረም 19 2015 ዓም, https://www.amnesty.org/en/documents/asa16/5933/2022/en/

7 አምነስቲ ኢነተርናሽናል፥ ከዘካሪያስ ዘላለም ጋር ሚያዚያ 12 2015 ዓ.ም ካደረገው የቪዲዮ ቃለ-መጠይቅ የተወሰደ

አስተዋጽኦ እያደረገ እንደሚቀጥል ከፍተኛ ስጋት አለ። ጥላቻን የሚያበረታቱ እና ሁከትና ዘረኝነትን የሚቀሰቅሱ መልዕክቶችን ከፍ-ከፍ በማድረግ፣ የሜታ አልጎሪዝሞች በዓለም ዙሪያ ያሉ ማህበረሰቦችን ሊጎዱ እንደሚችሉ ጥርጥር የለውም፤ ይህ ደግሞ በብዛት እየጎዳ ያለው ትኩረት የተነፈጋቸውን ማህበረሰቦች ነው።

ሜታ፣ከሲቪል ማህበረሰቡ በርካታ ማስጠንቀቂያዎች የተሰጡት ቢሆንም፤ ስህተቶችን እንደማይደግም እሱ እራሱ ማረጋገጫ የሰጠ ቢሆንም፤ ቀደም ሲል ሌላ ቦታ የፈፀማቸውን ያሰራር ግድፈቶች ኢትዮጵያም ውስጥ ደግሟቸዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ በተከሰተው ጦርነት ሜታ የሰጠው ምላሽ የሚጠበቀውን ያህል ያልነበረ እና ማይናማር ላይ ያሳየው ድክመት ነፀብራቅ ከሆነ፣ እየተከተለው ባለው የቢዝነስ ሞዴል የተነሳ የሚፈጠሩ ችግሮችን ኩባንያው የመፍታት አቅም እንደሌለው የሚያሳዩ አሳዛኝ ማስረጃዎች ናቸው። ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት በሌለበት ሁኔታ፣ ኩባንያው ዛሬም እንደትናንቱ ችግሮችን መፍታት እንደማይችል አሳይቷል። በመሆኑም፣ ለሶስተኛ ጊዜ ተመሳሳይ ስህተቶችን እንዲሰራ ሊፈቀድለት አይገባም።

ሜታ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚጠቀመው የንግድ አሰራር ስልት የተነሳ ለሚያደርሰው ጉዳት እውቅና አለመስጠቱ ወይም ሀላፊነት አለመውሰዱ፣ ኩባንያው ከይዘት መፈረጅ አልጎሪዝሞቹ ጋር የተቆራኙ ጉዳቶችን በበቂ ሁኔታ እና በብቃት ለማቃለል አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችን የማድረግ አቅም እንደሌለው ወይም ለማድረግ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ግልፅ እየሆነ መጥቷል። ሜታ፣ በቂ የመልዕክቶች ይዘት ተቆጣጣሪዎችን በማዘጋጀትና ከሲቪል ህብረተሰቡ ጋር ያለውን ግንኙነት ይበልጥ ትርጉም ባለው መልኩ በማሳደግ፣ የሰብአዊ መብቶችን የማክበር ሀላፊነቱን ለማሻሻል በኢትዮጵያ እና በሌሎች ስራውን በሚያከናውንባቸው ሀገሮች ሁሉ አሰራሩን በፍጥነት ለመቀየር ጥረት ማድረግ አለበት።

ያልተገራው የትላልቅ ኩባንያዎች እድገት፣ በመላው ዓለም፣ ሰብኣዊ መብቶች አጠባበቅ ላይ አሳሰቢ ችግሮችን አስከትሏል። በትላልቅ ኩባንያዎች የሚፈፀሙ የሰብኣዊ መብት ጥቃቶችን ለመከላከል እና አጥፊዎችን ለመቅጣት የሚያስችሉ ድንጋጌዎችን ማውጣት እና የቁጥጥር ስርዓቶችን መዘርጋት፣ መንግስት የሰብኣዊ መብቶችን ለመጠበቅ ከሚፈፅማቸው ተግባራት መካከል ዋነኞች ግዴታዎቹ እና ሀላፊነቶቹ ናቸው። የተጠቃሚዎችን ዱካ የሚከታተል የንግድ ሞዴልን ለመቆጣጠር የሚያስችል ድንጋጌ ማውጣትና ማስፈፀም፣ መንግስታት የዜጎቻቸውን ሰብኣዊ መብቶች ለማክበር ከሚፈፅሟቸው ግዴታዎች መካከል ከመቸውም ጊዜ በላይ ቁልፍ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል።

# ምክረ-ሃሳቦች

## ለሜታ

### ኢትዮጵያ ውስጥ ወደፊት ሊደርስ ስለሚችል ጉዳት መፍትሄ እና መከላከያ

- ፌስቡክ ላይ በተሰራጨው የጥላቻ ቅስቀሳ የተነሳ በቀጥታ የተጎዱትን አብርሃም ማዕረግን፣ ፍስሀ ተክሌን እና ሌሎች ግለሰቦችን ጨምሮ በኢትዮጵያ ለደረሰው የሰብአዊ መብት ጥሰት ሜታ ስላደረገው አስተዋፅኦ በይፋ እውቅና ይስጥ፤ ይቅርታም ይጠይቅ።
- እነዚህ ጉዳቶች ወደፊት ዳግመኛ እንዳይደገሙ ለማረጋገጥ፣ ተሳትፎን መሰረት ያደረገውን የንግድ ሞዴሉን ለመቀየር ቁርጠኛ ይሁን።
- ለሰሜን ኢትዮጵያ የግጭት ተጎጂዎች እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በግጭት ለተጎዱ ቡድኖች የሚውል የካሳ ክፍያ ፈንድ ይመድብ።
- የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች በመልዕክቶች ይዘት ላይ ይበልጥ ትርጉም ያለው ግብዓት እንዲሰጡ በመፍቀድ፣ በኢትዮጵያ ‘የታመነ አጋር’ ፕሮግራምን ያሻሽል።
- የሰብአዊ መብት የደረጃ መስፈርቶችን ለማክበር በሚስያችሉ ሁኔታዎች ለመስራት ቁርጠኛ የሆኑ ተጨማሪ የመልዕክት ይዘት ተቆጣጣሪዎችን በቀጥታ መቅጠርን ጨምሮ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ በሚውሉ 84 ቋንቋዎች የቁጥጥር አቅሙን ያስፋፋ።

### የሰብአዊ መብት ትጋት (due diligence)

- የፌስቡክ የክትትል ቦርድ ባቀረበው ምክረ-ሀሳብ መሰረት፣ ኢትዮጵያን በተመለከተ በተቻለ ፍጥነት ሁሉን አቀፍ የሰብአዊ መብት ተፅእኖ ግምገማ ያካሂድ፤ ያሳትም።
- በእያንዳንዱ ሀገር ለሚፈፀሙ የሰብአዊ መብት ረገጣዎች ሜታ ምንም አስተዋፅኦ እንደማያደርግ እየተወሰዱ ስላሉ የማሻሻያ እርምጃዎች ማረጋገጫ ከመስጠት በተጓዳኝ፣ ‘አደጋ ላይ ናቸው’ ተብለው በውስጥ የተለዩ ሀገሮችን ዝርዝር ያሳትም፤ በየጊዜውምዝርዝሩን ያዘምን።

- 'አደጋ ላይ ናቸው'' ተብለው በተለዩ ሁሉም ሀገሮች ውስጥ የሰብአዊ መብት ተጽኖ ግምገማን ያካሂድ፤ ግኝቱንም ይፋ ያድርግ።
- ሜታ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ የሰብአዊ መብት ትጋት ሂደቶች፣ ጠቅለል ባለ መልኩ፣ የሜታ የንግድ ሞዴል በሰብአዊ መብት ላይ ስለሚያስከትላቸው አሉታዊ ተጽኖዎች መፍትሄ እንደሚሰጥ እና አደጋዎች በግልጽነት በምን አኳኋን በቅድሚያ ተለይተው መፍትሄ እንደሚያገኙ ያረጋግጥ።
- የሚደረጉ የሰብአዊ መብት ተፅዕኖ ግመገማዎች ሁሉ አዳዲስ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (AI) ስርአቶችን እና የተሳትፎ መለኪያዎችን ከመንደፍ እና ስራ ላይ ከማዋል ጋር በተገናኘ ትርጉም ያለው ማህበራዊ መስተጋብር (MSI) እንዲያከናወኑ ያድርግ፤ በእነዚህም ላይ ትርጉም ያለው የህዝብ ምክክር እንዲካሄድ ያድርግ፤
- አዳዲስ ስርዓቶች እና የንድፍ ገፅታዎች የሚለቀቁበትና የሚተገበሩበት ጊዜ ጨምሮ፣ በአልጎሪዝም ቴክኖሎጂዎች ያሰራረ ዑደት ውስጥ ያለተቋረጠ፣ ቀጣይ እና ንቁ የሰብአዊ መብቶችን ጥንቃቄ ያድረግ፤ ይህም ቴክኖሎጂዎቹ እየተገነቡበት ባሉበት ደረጃም ሆነ ጥቅም ላይ ከዋሉ በኋላ አደጋዎችን እና ጥቃቶችን መለየት ያስችላል።

## የንግድ ሞዴል እና አልጎሪዝሞች

- የግላዊነት መብትን የሚጎዳ እና የተለያዩ የሰብአዊ መብቶችን አደጋ ላይ የሚጥል ወረራ-አከል የግል የመረጃ አሰባሰብን ያስቁም።
- የታለመ ማስታወቂያን መሰረት ያደረገ አሰራርን ያቋርጥ፤ ጎጂ ያልሆነ አማራጭ የንግድ ሞዴልን ይቀበል።
- የፌስቡክ ተጠቃሚዎች፣ የመስመር ላይ (ኦንላይን) አጠቃቀማቸው ላይ የበለጠ የቁጥጥር አቅም እንዲኖራቸው የይዘት መፈረጃ አልጎሪዝሞችን ለመጠቀም የሚያስችል 'መርጦ የመግባት' አማራጭ ያቅርብ።
- እንደ ዳግም ማጋራት፣ መልዕክትን ለሌሎች ማስተላለፍ እና የቡድን መጠን በመሰሰሉት ላይ ገደብ በማስቀመጥ፣ 'የ'ፍትገት' (friction') እርምጃዎችን የመደበኛ አሰራሩ አካል ያድርግ፤ እነዚህን ዘዴዎች በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ እንደ መስፈርት በመጠቀም 'የታማኝነት'(integrity') ውጤቶችን ለማሻሻል ውጤታማ ሆነው የተረጋገጡ እርምጃዎችን ይውሰድ።
- ከፍተኛ አደጋ በሚፈጠርባቸው አጋጣሚዎች 'መስታወቱን ሰባብር' በመባል የሚታወቀውን ቅፀበታዊ እርምጃ በንቃት ተግባራዊ ያድርግ።
- የመልዕቶች ይዘትን መፈረጃ እና መቆጣጠሪያ አልጎሪዝሞች አጠቃቀምን በተመለከተ ግልጽነትን በከፍተኛ ሁኔታ ያሻሽል፣ የእነሱንም አሰራር ቴክኒኮች በግልጽ ለመረዳት በሚያስችል መልኩ ለተጠቃሚው በይፋ ማስቀመጡን ያረጋግጥ ።
- ከአልጎሪዝም ስርዓቶች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ጨምሮ፣ ለህዝብ ጥቅም የሚውሉ መረጃዎችን ተመራማሪዎች እንዲያገኙ እና ጥናታዊ ዳሰሳ እንዲያደረጉ ያስችል።

## በዓለም-አቀፍ አብዛኛዎቹ ሀገሮች ውስጥ ፣ በተለይም 'ለአደጋ ተጋላጭ' በሆኑ ሀገሮች' የንግድ ሥራዎችን በተመለከተ

- በተለይ በእንግሊዝኛ ተናጋሪ ባልሆኑ ዓለም አቀፍ አብላጫ ሀገሮች መካከል ያለውን መበላለጥ ለማስተካከል፣ ያልተመጣጠነ ተጽእኖ የሚያሳድሩትን ችግሮች አስቀድሞ በመፍታት ረገድ ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ የአገር ውስጥ ቋንቋ ሃብትን መደገፍ ላይ በቂ ኢንቨስትመንት እንዲደረግ ያረጋግጡ።
- በዓለም አቀፍ ደረጃ፣ የመልዕክት ይዘት ግምገማን፣ የፖሊሲ እና የሰብአዊ መብት ቡድኖችን አቅርቦትን በተመለከተ በክልሎች መካከል ያለውን እኩልነት እና ወጥነት ያረጋገጡ።

# አሜሪካ፣ አየርላንድ እና እንደ አውሮፓ ህብረት ያሉ የክልል አካላትን ጨምሮ ለሜታ እንደ ዋና መቀመጫ የሚያገለግሉ መንግስታት

- የተጠቃሚዎችን መረጃ ሰርሳሪ በሆነ መልኩ የታለሙ ማስታዎቂያዎች ላይ ያተኮሩ አሰራሮችን ይከልክሉ።
- እንደ ፌስቡክ እና ሌሎች ተመሳሳይ የማህበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርሞች በጣም አስፈላጊ የሆኑ የዲጂታል አገልግሎቶችን እና መሠረተ ልማቶችን ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የማድረግ ስራ፣ የተጠቃሚዎችን ዱካ ያለማቋረጥ መከታተልን እንደ ግዴታ ያለስቀመጠ መሆኑን ያረጋግጡ። የዲጂታል አገልግሎቶችን እና መሰረተ-ልማቶችን ለህዝብ ተደራሽ የማድረግ ስራ፣ የፕላትፎርሙን ተጠቃሚዎች [ነፃ] ፍላጎት እና ስምምነት መሰረት ያደረገ መሆን አለበት። ይህ ደግሞ፣ የንግድ ማስታወቂያ ድርጅቶች እና ሌሎች

**"ለአባቴ የሞት ፍርድ"**

በሰሜን ኢትዮጵያ ለደረሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሜታ ያደረገው አስተዋጽኦ

አምነስቲ ኢንተርናሽናል

ሶስተኛ ወገኖች የተጠቃሚዎችን ዱካ እየተከተሉ እንዳያስቸግሯቸው ዋስትና መስጠት የሚያስችል ድንጋጌ ማውጣትን እና ተፈፃሚ ማድረግን ይጠይቃል። ወረራ-አከል ክትትል አንዳይደረግባቸው [ከፈለጉ]፣ተጠቃሚዎችን ክፍያ የሚጠይቁ የደንበኝነት አገልገሎት ሞዴሎች፣ ፈቃድ ሊሰጣቸው አይገባም።

- የማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች በሚሰጧቸው አገልግሎቶች እና በአገልግሎቶች አጠቃቀም ዙሪያ ተጠቃሚዎች ላይ ለሚያደርሱት [ስልታዊ] የሰብአዊ መብት ጉዳቶች መፍትሄ ለመስጠት ግዴታ ውስጥ እንዲገቡ ያድርጉ ።

- የማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎችን ጨምሮ፣ ኩባንያዎች የንግድ ስራዎቻቸውን፣ ምርቶቻቸውን፣ አገልግሎቶቻቸውን እና የንግድ ግንኙነታቸውን በተመለከተ  የሰብአዊ መብት ትጋት እንዲያደርጉ እና ስለ ትጋት ፖሊሲዎቻቸው እና አሰራሮቻቸው የዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ባሟላ መልኩ ሪፖርት እንዲያደርጉ በህግ አግባብ ይጠይቁ ።

- የኢንተርኔት ፕላትፎርሞች የመልዕክቶችን ይዘትን በሚቀርፁ አልጎሪዝሞች አማካኝነት ተጠቃሚዎችን እንዳሻቸው እንዳያደርጉ፣ በቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ላይ ቁጥጥር ያድርጉ፤ ቁጥጥሩንም ሲያደርጉ፣ ኩባንያዎቹ [ወደ ፕላትፎረሙ] መርጦ የመውጣትን (an opt-out) ሳይሆን፣ መርጦ የመግባትን (an opt-in) የስምምነት አማራጭ ተጠቃሚው አውቆት፣ በግልፅ፣ ያለክፍያ እና በማያሻማ መልኩ ማቅረብ አለባቸው። ከተጠቃሚው በቀጥታ ያልተገኙ መረጃዎች (inferred data) አሰባሰብ እና አጠቃቀም (ለምሳሌ፣ የምልከታ ጊዜ እና ላይክን መሰረት ያደረጉ ምከረ-ሀሳቦች) መታገድ አለባቸው። ከዚህ ይልቅ፣ ተጠቃሚወች፣ የትኞችን ጠቋሚዎች ወይንም የገለጿቸውን ፍላጎቶች ለፕላትፎሙ ከሚሰጡት መረጃ ጋር እንዲያጣጥምላቸው ሙሉ በሙሉ የመቆጣጠር ነፃነት ሊሰጣቸው ይገባል። በሚሰጡት መረጃ መሰረት የሚሰጥ ምክረሀሳብን የሚመርጡት ደግሞ፣ ፍላጎታቸውን ለፕላትፎርሙ በግልፅ፣ ያለክፍያ እና ተነግሯቸው በተስማሙበት መሰረት አማራጭ ሊሰጣቸው ይገባል።

- የቴክኖሎጂ ዘርፉን ገለልተኛ በሆነ መልኩ ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር እና ለማስተዳደር የሚያስችሉ ደንቦችን ለማውጣት፣  በቂ ኢንቨስትመንት እንዲኖር ያድርጉ።

- ከዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ህግጋት እና መስፈርቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ፣ በማህበራዊ ሚዲያ ኩባንያዎች የሚፈጽሙትን ጥሰቶችን በትክክል ለመመርመር እና አጥፊዎችንም ለመቅጣት ይችሉ ዘንድ፣ ብሄራዊ መረጃ ጥበቃ ተቆጣጣሪዎች ተፈላጊው እውቀት ያላቸው መሆኑን እና በቂ ሃብትም እነደተመደበላቸው ያረጋግጡ።  መንግስታትም፣ ስህተቶችን ለማስተካከል የሚረዱ የግል እና የወል ስልቶች መኖራቸውን ያረጋግጡ።

**“ለአባቴ የሞት ፍርድ”**

በሰሜን ኢትዮጵያ ለደረሱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ሜታ ያደረገው አስተዋጽኦ

አምነስቲ ኢንተርናሽናል

# አምነስቲ ኢንተርናሽናል ለሰብዓዊ መብቶች የቆመ ዓለምአቀፋዊ እንቅስቅሴ ነው። አንድም ሰው ላይ እንኳ የሚፈፀም ኢፍትሀዊነት


በዚህ ያግኙን

info@amnesty.org

+44 (0)20 7413 5500

ውይይቱን ይቀላቀሉ

www.facebook.com/AmnestyGlobal

@Amnesty

# ሁላችንንም ያገባናል።

ጠቋሚ፤ AFR 25/7152/2023
ህዳር 2016
ቋንቋ፡ አማርኛ

amnesty.org

AMNESTY INTERNATIONAL

# "በአባቴ ላይ የተፈፀመ ግድያ"

## በሰሜን ኢትዮጵያ ለተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የሜታ አስተዋፅኦበሰሜን ኢትዮጵያ ለተፈፀሙ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የሜታ አስተዋፅኦ

በህዳር ወር በ2013 ዓ.ም፣ በሰሜን ኢትዮጵያ እጅግ አሰቃቂ ጦርነት ተቀሰቀሰ። በ2013 ዓ.ም የመረጃ መንታፊዋ ፍራንሲስ ሃውገን እንደተናገረችው፣ ፌስቡክ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገሮች፣ " የጎሳ ግጭትን እንዲቀጣጣል" አድርጓል።

ይህ ዘገባ፣ ከ2013 እስከ 2015 ዓ.ም ድረስ በትግራይ ማህበረሰብ ላይ በተፈጸመው ከባድ የሰብአዊ መብት ረገጣ የሜታ ሚና ምን እንደነበረ የፈተሸ ጥናት ነው። በፌስቡክ ተጠቃሚዎች ተሳትፎ ላይ የተመረኮዘ የንግድ ሞዴል፣ በኢትዮጵያ የትጥቅ ግጭት ወቅት ያሳደረውን አስከፊ ተጽእኖ ሪፖርቱ ያሳያል። ምንም እንኳን ኩባንያው በ2009 ዓ.ም፣ ሮሂንጃዎች ላይ ለደረሰው ግፍ መባባስ ካደረገው አስተዋፅኦ ትምህርት ወስጃለሁ ቢልም፣ እየተከተለው ባለው አሰራር የተነሳ ኢትዮጵያ ውስጥም በድጋሚ ተመሳሳይ ጉዳቶች እንዳደረሰ ጥናቱ አሳይቷል።

በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ተጽእኖ ግምገማን እንዲያካሂድ፣ የራሱ የፌስቡክ ተቆጣጣሪ ቦርድ ምክረሀሳብ ያቀረበለት ቢሆንም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ለተፈፀሙት ከባድ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ የእርሱ ድርሻ ምን እነደነበር የሚየሳይ ግምገማን፣ ሜታ እስከ ዛሬ ድረስ አላደረገም። የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ትንታኔ ግን፣ የጉዳዩን አጣዳፊነት በሚገባ አሳይቷል፤ ከዚህ በተጨማሪም፣ ሪፖርቱ፣ ሜታ ኢትዮጵያ ወስጥም ሆነ በሌሎች የጉዳት ሰለባ በሆኑ አካባቢዎች ለሚፈጸሙ የሰብአዊ መብት ረገጣዎች አስተዋጽኦ ማድረጉን እንደማይቀጥል ለማረጋገጥ የሚያስችሉት ሰፋ ያሉ የማሻሻያ እርምጃዎች እና ትርጉም ያለው ደንብ ማውጣት እነዳለበት አስምሮበታል።

ጠቋሚ፤ AFR 25/7152/2023
ህዳር 2016
ቋንቋ፡ አማርኛ



AMNESTY INTERNATIONAL